## የዲሬክተሮች፡ቦርድ

**አቢዩ፡ፎርድ**

ሊቀ፡መንበር

**ታምራት፡ገብረመድህን**

**ያዕቆብ፡ሀይለማርያም**

**ፈንታሁን፡ጥሩነህ**

**ዋና፡አዘጋጅ**

ፈንታሁን፡ጥሩነህ

**የአዘጋጅ፡ቦርድ**

ክፍአለ፡ገብረ፡ጊዮርጊስ

ሙሉጌታ፡ከበደ

ሠይፉ፡በላይ

**የሥርጭት፡ሀላፊ**

አህመድ፡ኑር

**የአማካሪ፡ቦርድ**

ማይገነት፡ሽፈራው

(ሜሪላንድ - ሰሜን፡አሜሪካ)

ጌትነት፡በላይ

(በርሊን- ምዕ·ጀርመን)

ኢንዱ፡ቦናና

(ጣሊያን)

ጽሑፎችን፡በዚህ፡አድራሻ፡መላክ፡ይቻላል፡፡


**SEM INNA WORQ**

**P.O.BOX 43003**

**WASHINTON, D.C. 20010**

**USA**



ISSN: 0891-9119

Sem Inna Worq Corporation is a non-profit oganization.

Washington. D.C. U.S.A.

# ስምና ፡ ወርቅ

ጥር ፡ ፲፱፻፹ ዓ.ም ።    ቅጽ ፡ ፩ ፡ ቁጥር ፡ ፫

በዓመት ፡ ሶስት ፡ ጊዜ ፡ እየታተመ ፡ የሚወጣ ፡ መጽሔት ።

## ማውጫ

ገጽ ፡

ርዕሰ ፡ አንቀጽ ፡- ---------------------------------------- 1

ደብዳቤዎች ፡- ---------------------------------------- 6

የታሪክ ፡ ገፅ ፡- ---------------------------------------- 18

ከዶክተር ፡ ጌታቸው ፡ ኃይሌ ፡

የፊደል ፡ ገፀበረከት ፡- ---------------------------------------- 32

ከአቶ ፡ ተክለማርያም ፡ ሀይሌ ፡

አብዮት ፡---ከንድፈ-ሀሳባዊ ፡ ጥያቄ ፡ አንፃር ፡ (ክፍል ፡ ሁለት) ፡- ----- 44

ከአቶ ፡ ደሕረት ፡ መከስ ፡

የኢትዮጵያውያን ፡ ሳይንቲስቶች ፡ የሙያ ፡ ማህበር ፡ አስፈላጊነት ፡- ---- 63

ከአቶ ፡ ሠይፉ ፡ በካይ ፡

እንዴታ ! አከው ፡ እንጂ ! ፡- ---------------------------------------- 67

ከአቶ ፡ ጉ.ነ.ብልጣሶር ፡

" አልቦ ፡ ዘመድ " ፡- ---------------------------------------- 69

ከአቶ ፡ ብርሃኑ ፡ ድንቄ ፡

አውሬ ፡ ቡራቡሬ ፡ (ግጥም) ፡- ---------------------------------------- 73

ከአቶ ፡ ዲዲሞስ ፡ አባንራች ፡

የጥናት ፡ ሠነዶች ፤ ---------------------------------------- 77

የደረሱን ፡ መጻሕፍትና ፡ ጽሑፎች ፤

የደረሱን ፡ የፖለቲካ ፡ ጽሑፎችና ፡ መጽሔቶች ፤

የቃላት ፡ መፍቻ ፡- ---------------------------------------- 88

ምርምርና የምርምር ጥናት ለምን አስፈለገ የሚለውን ለመመለስ በኢትዮጵያ ተጨ
ባጭ ሁኔታ ለምርምር ሂደት ጠንቅ የሆኑ ባህሪዎችንና አሠራሮችን እንዲሁም ፀረ- ምር
ምር እርምጃዎችንና እምነቶችን በመጠኑ እንጠቅሳለን ። በቀድሚያ መተቸት የምንፈል
ገው "አንመራመር" በሚለው አሉታዊ አስተያየት ላይ ነው ። ያገራችን ባህል ለምርምር
በር የከፈተውን ያህል የምርምርንና የተመራማሪዎችን ጥረት ተስፋ የሚቆጭ ገፅታም
አለው ። በአንድ በኩል የአበውን አባባል መነሻ አድርገን ለገወስድ "መጠየቅ ያደርጋል
ሊቅ" የሚለውን መመራመርን ፣ መጠየቅን ፣ ማሰብን ፣ መተንተንን ፤ ...የሚያበረታታ
ምሳሌ እናገኛለን ። በሌላ በኩል ደግሞ የዚህ ተፃራሪ የሆነ በሃል ለፍኖ እናገኛለን ።
አንመራመር የሚለው ወገን ክስተቶችን ሆነ ማንኛውንም ነገር በጭፍን እምነት የሚቀበ
ልና የተቀበለውንም ያለገደች ጥያቄ የሚያስተጋባ ወይም በሥራ ላይ እንዲውል የሚጥር
ነው ። መጨረሻ ላይ ግን ሀሳብ አመንጪውና በጭፍን እምነት ተቀብሉ የሚያስተጋባው
ሰው ያላቸው ግንኙነት የእኩልነት ሳይሆን የበላይና የበታች ዝምድና ከመሆን አያልፍ
ም ። ዞሮ ዞሮ ሀሳብ አመንጪውና ተቀባዩ በአክብሮት የሚተያዩ አይሆኑም ። ጭፍን
አማኙ በቂልነት ፣ በየዋህነት የሚታይ ገዑስ ፍጥረት እየሆነ ይሄዳል ። በሰው ልጆች
እኩልነት ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ሲኖር ማንኛውም ሀሳብ ያለገደች ጥያቄና ሂሳዊ ትች
ት ፣ ያለገደች ግምገማና ትንታኔ እንዲያልፍ አይደረግም ። የምርምር ዘዴ የሚያውቀ
ተመራማሪ ይህን ዕውቀት የበላይነት መፈለጊያና ማፅደቂያ ለማድረግ ከመሻት ይልቅ ያለ
ውን ሳሳወቁት ለማዳረስ ያልተቀጠበ ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል ። ሆኖም ደግሞ ለአ
ንድ የምርምር ዘዴ ሰጋጆች እንዳይሆኑ ሰዎች እንዲተቹበት መጋበዝ ፣ ማበረታታት ተገ
ቢ እርምጃ ነው ። በዚህ ዓይነት ሂደት ማንም ሰው ፍጹም አዋቂ ማንም ደግሞ ፍጹ
ም አላዋቂ ሆኖ አይተያይም ። የመከባበር ፣ የመመሳሰል ፣ አብሮ የማደግና አብሮ
የመኖር ዝንባሌ ሊጠነክር የሚችለው ይህ ሲሆን ይመስለናል ። ባገራችን አንመራመር
የሚለው አስተሳሰብ ጉልቶ የሚታየው ቀኖናዊ አስተሳሰቦች ሰፍነው በሚገኙበት አካባቢ
ነው ። ግትር አስተሳሰቦች ለምሳሌ አንድ ዓለም ፣ አንድ ሀሳብ ፣ አንድ ዓይነት አስተ
ሳሰብ ፣ አንድ ርዕዮተ-ዓለም የሚል "አንዳዊ" አስተሳሰብ ቀኖናዊ መንገድን ሊከተል
ቀይቷል ። በሌላ በኩል ደግሞ ፣ "ፍጹማዊ" አስተሳሰቦች ለምሳሌ ያህል ለመጥቀስ ፍጹ
ም እውነት ፣ ፍጹም አንድነት ፣ ፍጹም ውህደት ፣ ፍጹም ጠባት ፡...የመሳሰሉት ሲገሸ
ራሽሩና ያለምርምር ያለተችት ፣ ያለጥያቄ ሲታመንባቸው ቀይተዋል ። እነዚህ ቀኖናዊ
አቀራረቦች የሚያገለግሉት በጭፍን እምነት ላይ ሕልውናቸው ለተመሠረቱ ተቋሞችና
አቋሞች ብቻ ነው ። ተለዋዋጭ በሆነው ዓለም ላይ ፣ ማንኛውም ክስተትና ኢክስተት
ሁሉ የማያቋርጥ እንቅስቃሴና ለውጥ በሚያደርግበት ጊዜ አንዳዊና ፍጹማዊ ቀኖናዊ
ግትር አቋሞችና የአስተሳሰብ ፈለግ ውጤቱ አሉታዊ ነው ። መመርመር ፣ መጠየቅ ፣
መፈለግ ፣ መተቸት ፡... በ"ሀቅና" በ"እውነት" መካከል ያለውን ልዩነት ፣ ቀኖናዊና ቀኖ
ናዊ ባልሆኑ ተንቀሳቃሽ (ተችታዊ) ወይም "ሳይንሳዊ" አስተሳሰቦች መካከል ያለውን ልዩ
ነት ለማጥበብ የሚረዱ መሣሪያዎች ናቸው ። ሆኖም ምርምርና የምርምር ውጤት ለሰ
ው ልጆች እኩልነትና እኩሳዊ ተሣትፎና ጥቅም እንዳያገለግል ከተደረገ የሚያስከትለው
ጥፋት የዚያን ያክል ይሆናል ። ምርምር የተመራማሪዎችን ተህትናና በጐ ፈቃድ ይጠይ
ቃል ፤ አለዚያ የማጥቂያ ፣ የመግዣ ፣ የበላይነት... መሣሪያ ከመሆን አያልፍም ። ጭፍ
ን እምነት አማኞችም የምርምር ሂደት እንዳይጐለምስና እንዳያብብ የሚያግዙ ሀይሎች
ከመሆናቸው ሌላ አምባገነንነትን ፣ ጭቆናን ፣ ኢምክንያታዊና ፀረ-ዲሞክራሲያዊ ርምጃ
ዎችን የሚያራምዱ ወገኖች ወደመሆኑ ይገፋሉ ።

አንመራመር የሚለው አመለካከት ጭፍን እምነትን መሠረት ያደርጋል ስንል እነዚህ

እምነቶች ምን እንደሚመስሉ አንዳንድ ማስረጃ ለማቅረብ እንሞክራለን ። ለምሳሌ ያህል "ዝንብ አፉ ውስጥ ገባች ጠላ ልጠጣ ነው " እና "እንቅፋት መታኝ ላይቀናኝ ነው " የሚሉ ዓይነት እምነታዊ አስተሳሰቦች ምክንያት አዘል እንደልሆኑ መገንዘብ አዳጋች አይደለም ። ለሚያምንበት ሰው ግን ቀጥተኛ የሆነ ትርጉም አለው ። ሆኖም የነዚህ እምነቶች መነሻና መድረሻ ቢጠና ምናልባት ቀጥተኛ ትርጉማቸውንም ባይሆን በጀርባቸው ያለውን ምክንያት መረዳት ይቻል ይሆናል ። ሌላው ዓይነት ድምዳሜ ደግሞ መመርመር ጨርሶ ፋይዳ እንደሌለው ለማስረዳት የሚሞክር ነው ። ለምሳሌ "ከፀሐይ በታች አዲስ ነገር የለም " የሚለው አባባልና "ተመራምረን የት እንደርሳለን" የሚለው አባባል ሁለቱም ተደጋግመው የሚነገሩ አስተያየቶች ናቸው ። የነዚህ አስተያየቶች ምንጭ የተለያየ ቢሆንም በሕብረተሰቡ መካከል ተመሳልሰው ሲነገሩ ወደ እምነት ተለውጠው ሕብረተሰቡ የምርምርን አስፈላጊነት ጨርሶ እንዳያይ ኬላ ይፈጥራሉ ። የነዚህ አባባሎች ጀርባ ቢመረመር ጠለቅ ያለ ትርጉም እንደሚኖራቸው በመዘንጋት አይደለም ። ስለዚህ አስተያየቶችንና ባህላዊ አባባሎችን ደርቀው እንደቆሙ ክስተቶች በመቁጠር በአምልኮ ወይንም በጭፍን እምነት ከመመልከት ይልቅ አበው የሠጡትን ምሣሌ ተከትለን "መጠየቅ ያደርጋል ሊቅ" በሚለው ጉዳና ለመጓዝ ሚዛናዊ የሆነ ተችታዊ (ሂሳዊ)አቀራረብን ስንቅ ማድረግ ይኖርብናል ።

በሁለተኛ ደረጃ ማገሣት የምንፈልገው ነጥብ መጽሐፍ ላይ የሠፈረው ሀሉ ወይንም አንድ ታዋቂ ሰው የተናገረው ሁሉ የማይሻር ፣ የማይሻሻል ፣ የማይተችበት ... አድርጐ የመውሰዱ ባህል ላይ ያተኰረ ነው ። አንዳንድ ክርክሮችን ለመርታት ማመሳከሪያ የሚሆኑት እነዚሁ ናቸው ። በሀሳቡ ላይ ተጨባጭ ምሣሌዎች ፣ ተመክሮዎችና ማስረጃዎች ከማቅረብ ይልቅ መጽሐፉ የሚለውን ወይንም አዋቂ ሰው የተናገረውን ማሥረጃ በማድረግ የመርታቱ ወይም የተቃራኒውን ሰው አፍ የመዝጋቱ ባህል አሁንም የሚሠራበት ዘዴ ነው ። ምርምራዊ ዘዴ ይህን ዓይነት ዘዴ ተቃርኖ ቆሟል ። ምርምራዊ ባህል የያንዳንዱን ሰው ማንነት ከፍተኛ ቦታ ይሰጠዋል ። አዋቂ ሰው መከበር ያለበት ቢሆንም ፣ መጽሐፍ መጠቀስ ቢኖርበትም ሁለቱንም በአምልኮ ደረጃ ማየት ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝነ ነው ። የተጋነነ አመለካከት ጥቂቱን ሲጠቅም አብዛኛውን ይጐዳል ። ይህም ማለት አንድ ታዋቂ ሰው የሚለውን የሚያስተጋቡና ሁልጊዜ የሚደግፉ ሰዎች በዚያ ታዋቂ ሰው ጥላ ሥር የሚያገኙት ጥቅም በመኖሩ ያ ሰው እንዲመለክባቸው ይሻሉ ፤ በዚህን ሂደት ወቅት ያን ታዋቂ ሰው የሚቃወም ግለሰብ ሆነ ቡድን ወዲያውኑ የከረረ ቅራኔ ውስጥ ያስገባቸውና ፈጥነው መሣሪያ ወደ መማዘዝ ደረጃ ይደርሳሉ ። መጽሐፉን መጥቀስ የሚያምነውም ሰው በተወሰነ ደረጃ ይህንን መሳይ ተፅዕኖ በብዙ ሰዎች ላይ ያሳድራል ። ምርምራዊ ፣ ተችታዊ ፣ ትንተናዊ ባህል ግን የሀሳቦችን መፋጨትና በሂደቱም ወቅት የሚነሡ ቅራኔዎች በሰላማዊ መንገድ የሚፈቱበትን ዋስትና አብሮ ይዞ ይጓዛል ። ሀሳቦች በሚፋጩበት ወቅት ግለሰቡ ቀጥታ እንዲመታ ሆን ብሎ የሚሠነዝረው ያክርክር ነጥብ ስለማይኖር ተከራካሪዎች የተነሡበትን ነጥብ መፍትሄ ለመሻት ነፃ በሆነ መንፈስ ይከራከራሉ ። ተከራካሪዎችን ሆን ብሎ ለማሳፈር የሚነሣ ክርክርም ቢኖር በምክንያት አዘል ክርክር ፋርሽ ስለሚሆን ለምን ይህ ነጥብ ተነሣ ብሎ ቅር የሚያሰኝ አይሆንም ፣ ወይንም አያኰራርፍም ። ስለዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያለ ጥቅስ ሆነ ታዋቂ (አዋቂ) ሰው የተናገረው ቃል ለማስረጃነት በሚቀርብበት ጊዜ እንደፍፁማዊ የማይሻር ቃል አድርጐ መውሰድ መጽሐፉ የተጻፈበትን ዓላማና የአዋቂውን ሰው ዕውቀት የሚያፋልስ ስለሆነ በተገቢው መንገድ የመጠቀምን ባህል ማሳደግ ይኖርብናል ።

በሶስተኛ ደረጃ ማንሳት የምንሻው "ማወቅ አደጋ ነው " የሚለውን ፀረ-ምርምር አ

ለተያየት የሚመለከት ነው ። አንድ ግለሰብ ወይንም ቡድን ዕውቀትን በገበየ ቁጥር ፣
አዲስ ነገር በፈጠረ ጊዜ ሊከበርና ሊመሠገን ይገባል እንጂ ሊቀጣበት ወይም ሊንኳሰስ
በት አይገባም ። ባገድ ሕብረተሰብ ውስጥ ዕውቀትን ተፃረው የቆሙ ሀይሎች መኖራቸ
ውን አመልካች ነው ። ዕወቀት ለምን እነዚህን ሀይሎች ያሰጋቸዋል ቢባል ምክንያቱም
ረግቶና ፀንቶ የቆየው ባህል ለነርሱ መሰንበቻ ፣ የሀይላቸው ዋስትና ስለሆነ ብቻነው ።
አዲስ ነገር ፣ አዲስ ባህል የነዚህን ሀይሎች ምቾት ያናጋዋል ። እነርሱም የብዙሀኑን
ጥቅም ወይም የምልዐተ-ህዝቡን ዕድገት ለለማይሹ የራሳቸውን መደላደል ብቻ ትኩረት
ሠጥተው ይከናከናሉ ። ስለዚህም ከእውቀት አመንጪዎች ፣ ከእውቀት አስፋፊዎች ፣
ከተመራማሪዎች ጋር ያላቸው ዝምድና በተፃራሪ ቀራኔ የተመላ ይሆናል ። በዚህ ምክን
ያት ተመራማሪዎች ላይ የተለያየ ተፅዕኖ ማሳደር ይጀምራሉ ፤ ተመራማሪዎችም ተፅዕ
ኖው ሲበዛ ለምን አወቅን ወደማለተ ፀፀት ሊገፉ ይችላሉ ። ይህ ዓይነት አደጋ ብዙው
ን ጊዜ በመንግሥትና በተመራማሪዎች መካከል ያለውን ዝምድናና ቀራኔ ያመለክታል ።
ተመራማሪዎች ፣ አዋቂዎች ፣ ተቺዎች ነፃ የሆነ መድረክ ያስፈልጋቸዋል ። መንግሥት
በቁጥጥሩ ሥር ሊያውላቸው ከሚሻ ይልቅ ድጋፍ እየሠጠ ምርታማና ፈጣሪ ዝንባሌአቸው
እንዲያድግ ቢያደርግ ለሕብረተሰቡ በሙሉ የሚሠጡት ጠቃሚነት የላቀ ይሆናል ። የምር
ምራቸውን ውጤት በሥራ ላይ ለማዋል ዋስትናና ድጋፍ ካገኙ ደግሞ ለምርምር ጥናት
ጥብቅ አቋም ይዘው ያለሥጋት እንዲቀጥሉ ይረዳቸዋል ። ያወቁትንም ዕውቀት በጥቅም
ላይ በማዋላቸው ግላዊ ደስታና እርካታ ይሠማቸዋል ፣ ብሎም ደግሞ ለሕብረተሰብ ዕድ
ገት የሚሰጡት ጥቅም እየላቀ ይሄዳል ። በከፍተኛ ደረጃ በመንግሥት ተቋሞች የሚካ
ሄዱ የምርምር ጥናቶች የተመራማሪዎችን ግላዊ ስሜት የጠበቀ ፣ ለምርምር ማስኬጃ
የሚፈለገውን ቁሳዊና የበጀት ድጋፍ ያሟላ እንዲሆን ይጠበቃል ። በግለሰቦች አነሳሽነት
የሚካሄዱ የምርምር ጥናቶች ደግሞ ከላይ እንደጠቀስነው ነፃ የሆነ ፣ ተፅዕኖና ፍራቻ
የሌለበት አካባቢ ያስፈልጋቸዋል ። በተለይ ሀገራችን ውስጥ ያሉ እክሎችን ለማስወገድ
በጥናትና በምርምር መክበብ የጊዜው ግዴታ ነው ። ማወቅ አደገኛ ነው የሚል አስተሳ
ሰብ እንዳይዛመትም ማወቅ ፣ መመራመር ፣ መጠየቅ መፈለግ ፣ መፍጠር ...ተግባር
ላይ ያሉ ሙያተኞች ተገቢው ክብርና እንክብካቤ ያስፈልጋቸዋል ፤ የማወቅ ፍራቻ የሕ
ብረተሰብ እድገትን ፣ የግለሰቡንም ህልውና የሚፃረር ነውና ።

በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ለምርምር ጥናት መራመድ እክል ሆነው ከቆዩት ተግባ
ሮች መካከል ያገዳገዱቱ ምሁራንና ሊቃውንት አመለካከት ነው ። በተለይም ከውጭ
ተምረው ሀገሪቱን ማገልገል የሚገባቸውን ክፍሎች ይመለከታል ። ቀደም ብለን ካነሣ
ናቸው ቃለ-አጋኖአዊና ጽንፋዊ አስተያየቶች አንፃር ሲታይ አንዳንድ ከፍተኛ ትምህርት
የተማሩ ኢትዮጵያውያን ሀገሪቱ ልትንከባከባቸው የማትችል ፣ ለተማሩት ትምህርት የማት
መጥን ፣...አድርገው ይመለከታሉ ። ኢትዮጵያ ኋላ-ቀር ስለሆነች ሀገሪቱ ከምትፈልገው
በላይ ተምሬአለሁና ወደሀገር መመለስ ጥቅም የለውም የሚሉም አሉ ። ይህን አመለካ
ከት ሀገር በመካድ ደረጃ ባናስቀምጠውም ባስተሳሰብ ደረጃ ግን ትክክለኛ እንዳልሆነ መ
ጥቀስ ተገቢ ይመስለናል ። አያንዳንዱ ምሁር የሀገሪቱ ሁኔታ ምቹ ሆኖ እንዲጠብቀው
ሲመኘና ሲጠይቅ ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ ሆነው ይቀራሉ ። ከምርምራዊ ጥናትና
ሥራ መስፋፋት አንፃር ስንመለከተው ለሀገሪቱ የሚያስፈልጋት የሰለጠነ የሰው ሀይል አቅ
ጣጫው ወደውጭ እየሆነ ተራቁታ መቅረቷን መገንዘብ ይቻላል ። ኋላ-ቀርነትን ከሚያ
ስከትሉት ነጥቦች አንደኛው ይህ ቀራኔያዊ ክስተት ይመስለናል ። ሀገሬ ለኔ ምቹ ሆና
ትጠብቀኝ ከሚል አመለካከት ከመነሳት ይልቅ ሀገሪቱን ለምልዐተ-ሕዝቡ ምቾት ለማዘጋ
ጀትና ለማላደግ ምን ሳድርግ ብሎ አያንዳንዱ ምሁር ራሱን ዝቅ ማድረግ ይጠበቅበ
ታል ። ይህ ሳይሆን ቢቀር "አለቅጥ ተምሬአለሁ "የሚለው ምሁር መጨረሻው የስደት

# ደብዳቤዎች

ለሰምና ወርቅ አዘጋጆች፡-

መጽሔታችሁን ከመጀመሪያ ጊዜ አግኝቼ ሳነብ የተሰማኝ ደስታና ለአናንተም ክብር የምችለውን የሞራል ድጋፍ፣እንዲሁም ለከፈታችሁት የምርምርና የውይይት በር ምስጋናዬን ለማቅረብ በዚች አጭር ደብዳቤ ሁሉንም ለመግለጽ አዳጋች ቢሆንም ካደረጋችሁት የማቀራረብ አስተዋጽኦ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ እላለሁ። የአገራችን ታሪክና የሕብረተሰባችን ሁኔታ በነፃ መድረክ በቀን ክቦና ሃሳባቸውን ለመግለጽ ሁልጊዜ ለሚአልሙ ወጣት ኢትዮጵያውያን አንዱ እንደመሆኔ መጠን ሰኔ 1979 ዓ.ም በወጣው እትማችሁ "አብዮት፣ሶሻሊዝምና መንግሥት ከንድፈ ሐሳብ ጥያቄ አንፃር" በሚለው ርዕስ ላይ መሠረታዊ ትንታኔዎች አድናቆት ቢያድርብኝም እንኳ፣ በአንዳንድ ነጥቦች ላይ የተለየ አስተያየት ስላአደረበኝ ይህችን አጭር አስተያየት ለማቅረብ ዕድል እንዲሰጠኝ እጠይቃለሁ።

የኔ ልዩነት በሰኔው ጽሑፍ ይዘት ላይ ሳይሆን አብዮት ተካሄዷል ወይስ አልተካሄደም በሚለው ነጥብ ላይ ነው። በአጭሩ አብዮት የሚለውን ቃል ለመተርጎምና ለማብራራት ስንፈልግ ከግዕዝ፣ከማርክስና ኢንግልስ፣ ከሌኒንና ከሌሎች ፈላስፋዎች የተገኙ ቃላትና ሐረጎች እንዲሁም ከሌላ ሀገሮች የተገኙ ተመክሮዎች መንደርደሪያ ነጥቦች ሊሆኑ ቢችሉም እንኳ ውሳኔ ላይ ለመድረስ የምንችለው በአገሪቱ ውስጥ ይንፀባረቁ የነበሩ የኢኮኖሚ የፖለቲካ ሁኔታን የህብረተሰቡን ታሪካዊ የእድገት ደረጃ መንደርደሪያ ነጥብ በማድረግ ላይ ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ ባለፈው የፊውዳል ሥርዓት ተከፋፍሎ የተገዛ ከመሆኑም በላይ ህብረተሰቡ መሠረታዊ የኃራ ኑሮ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ተቋሞች አስከሌት

ህሊናቸው ኋላ ቀር በሆኑ ሠራተኞች ከሰላሳ ሚሊዮን በላይ የሚሆን ደምራ የሚል አቋም ነበራቸው እንጂ የኢትዮጵያ ታሪክና ባህል የሚያኮራ መርህ አልነበራቸውም። ነገሩን ባጭሩ ከመደምደም ወታደሩ ያለፈው ጨቋኝ የገዥ ክፍል ጥሎት ያለፈውን ባዶ ቦታ ሞላ ከማለት ያስደፍራል። ከሀገር ወዳድነት ስሜት ወደ ኮሙኒስት አዝማሚያ ያዘነበለውም የምዕራብና የምሥራቅ አውሮፓ የኮሙኒስት ፓርቲ አባል የሆኑ ግለሰቦች ወደ አገሪቱ መጉረፍ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶና (እነዚህ ሀይሌ ፊዳ ያሉ ሰዎች) የመኢሶንንና የኢሕአፓ የፖለቲካ ንትርክና የርስ በርስ ጦርነት ከፈነዳበት ጊዜ አንስቶ ነው።

ከዚህ በላይ የዘረዘርኳቸው ነጥቦች የአሁኑን ቢሮክራሲያዊ ወታደራዊ መንግሥት ሽፋን የሚሰጡ ሳይሆን ወይንም ባለፉት ዓመታት የተደረገውን ጭፍጨፋና ሽብር የሚክዱ ሳይሆኑ ያለፈውን ታሪካችንንና ያሁኑን ሁኔታዎች አጣምረን ያገራችንን ሁኔታዎች በመከታተል ሕሊናችን እንዲዳብርና የአገር ወዳድነት ትክክለኛ ምሁራዊ ባህል ለማሳደግ ይረዳል ብዬ ስላመንኩ ነው።

እንደ **የሰምና ወርቅ** አንባቢ በአንባቢዎች የደብዳቤ አምድ እንደገለጸው (ነአምን ዘለቀ፣ ሰምና ወርቅ ቅጽ ፩ ቁጥር ፬) ሁልጊዜ ስልጣን የያዙትን ግለሰቦች ከመንቀፍ ይልቅ የአገሪቱን ታሪካዊ ዕድገትና ተጨባጭ ሁኔታዎችን ብንመረምር የተሻለ ነው።

ጌታቸው መኳንንት
ቶሮንቶ/ካናዳ
ነሐሴ 6 ቀን 1979 ዓ.ም።

ከሰምና ወርቅ አዘጋጆች፣

"ሳንሱር አፍኖ ከያዛቸውና መተንፈሻ ቀዳዳ ሲፈልጉ መከስተኛ ደል ካገኙት የሕብረተሰብ ክፍሎች መካከል የተማረውን ክፍል እናነሳለን"[1] የሚለው ታሪክ ትዝታ በዚሁ መጽሔት ባለፈው እትም ርዕስ አንቀጽ መውጣቱ ሚከፊያ ነው።

የተጠቀሰውን መከስተኛ አጸክ ከሚሠገኘት መራራ ጸዋ የተቀበሉ ብዙ ወገኖች የከፍተህ ወሀኒ ተግከዋል። "ከአንጸ ሦስት ጊዜ የህል (ጥቃቅኑን ሳልቆጥር) አለአግባብ በታሰርኩበት ወቅት ከደረሱብኝ ከፍተኛ በደሎች ዋና ዋናዎቹ፣ በሞራሌ ላይ የደረሰብኝ የማይጠገን ስብራትና በአካላዊ የጤንነት ይዞታዬ ላይ ያስከተለብኝ የማይሻር ጸዊ ይኙባቸዋል"[2] ይላሉ በየጊዜው የደረሰባቸው ብደል ያንገፈገፋቸው ደራሲ።

በተለይም ከ1950 ዓ.ም በኋላ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተማሪዎች ማኅበር ከተቋቋመ ጀምሮ የነበረውን ስርዓተ መንግሥት የሚያወግዙ ጽሑፎች በአያሌ ተሰራጭተዋል። በአደባባይም ተነበዋል።

"ቀማር ጨዋታ ተጫውቼ፣
አጠብጥቤ ቀረሁ ተረትቼ።
ምነው ዕጸሌ በሰመረ፣
ዘውዱን ገልብጬ በነበረ"[3] የሚሉ ዓይነቶች በየጊዜው ተጸርሰዋል።

"--በስነ ጽሑፍ ባሕል በማራመድ በኩል በሀገሪቱ ውስጥ--- በትምሕርት ላይ የነበሩ ተማሪዎች አዎንታዊ አስተዋጽኦ"[4] ካደረጉት መሐል አንዱ ገሞራው በሚል የብዕር ስም የሚጠሩት አቶ ኃይሉ ገብረ ዮሐንስ ናቸው። አቶ ኃይሉ ከተማሪ ቤት እንዲባረሩ፣ ከዚያም ዓከም በቃኝ እንዲማቀቁ ካስደረጋቸው፣ በጊዜው "በረከተ መርገም" በሚል ርዕስ ከጻፉት ግጥም ከመጥቀስ፡-

"አልሰማሽ እንደሆን አልገባሽ እንደሆን ምድር የኛ አደራሽ፣
ስላቀፍሽው ፍጡር ያለውን ዓላማ ምናምንቴ ሐሳብ
እንዳንዱን ልንገርሽ"።
አዎን እንዲህ ይልልኛል፤
ካፈርሽ ሰው ሆኖ፤ ኋላም አፈር ሲሆን የሚሆንሽ አካል። "
"--- ደሀ ጌታ ሆኖ ከመግገብ ከበቃ
የቁንጫ እንጀት ማንን ተመገቦ፤ እንደምን ይጠርቃ?

- - - - - - - - - - - - - - - - -

ሺ አዋጅ ዳቦ ይሆን ይመስል፣ በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ከተከሰፈበት ነገር እንደ ባዶ ቃላት ከተራበ ሕዝብ እንደ መፍቲሀ መቅረብ ነው። በየጊዜው ስለሚወጣው አዋጅ መብዛት ሁለት የደርግ አባሎች ሲወያዩ፣

አንደኛው የደርግ አባል "ይህ አዲስ የምንለው አዋጅ ባለፈው ሳምንት የወጣነው አይደለም እንዴ? ሕዝብ ቢጠይቀን ምን እንመልሳለን?" ሲል ሁለተኛው የደርግ አባል ይመልስና "ሕዝቡ እንደሆነ ደንዘዘ ምንም አይከየው። አንተ እንዳልከው ጥያቄ መጠየቅ ከጀመረ ጥያቄ የሚጠይቅ ይረሸናል የሚል አዋጅ እናወጣለን" አሉ ይላል የአዲስ አበባው የመርካቶ ቀልድ።

አቶ በዓሉ በኦሮማይ መጽሐፋቸው ሰበብ በሕይወት የሉም የሚሉ ግለሰቦች አጋጥመውናል። የነገሩን እውነተኛነት ከማረጋገጥ በደብዳቤና በቴሌፎን ወደ ኢትዮጵያ የደረግነው ጥረት አልተሳካም።

ሳንሱርን አልፈው ከ1966 ዓም በፊት በገበያ ከዋሉት ግሩም ድንቅ የልብ ወለድ መጽሐፎች አንዱ **ፍቅር እስከ መቃብር** ነው። ይህ መጽሐፍ ከነበረው ሥርዓት ጥሩ መስታዎት ነው። **ከፍቅር እስከ መቃብር** ለመጥቀስ፣

"የንጉሥ ግብር ዛሬ እንዳየሁት ከሆነ ጥራሽ
አያሥመኝም ከድሀ ቤት ተከምና የሚበላው
ቁራሽ በስንት ጣዕሙ !---

የንጉሥ ግብር ! ግብር መቼም ዕዳ ነው
ታዲያ ንጉሥ ዕዳ ይከፍላል? የለም ሕዝብ ነው
ከንጉሥ ዕዳ የሚከፍለው። ----

ህዝብ ከንጉሥ የሚከፍለው የክብር ዕዳ ነው !
ሕዝብ ከሰውነት ወደ እንስሳነት ደረጃ ራሱን
ዝቅ አድርጐ ተገፍቶ ተመትቶ የሰውነት መብቱን
ክብሩን ሁሉ ትቶ የማይበላ ነገር በልቶ ተንቆ
ተደቅድቆ ከንጉሥ የሚገዛ መሆኑን የሚያሳይበትና
ንጉሱም ያን አየዩ ደስ የሚሰኝበት ዘዴ ነው !
ከሀብቱ ሀብት ከፍሎ እንደሚገብር ከሰውነቱ

ክፍሎ ከንጉሱ የሚገበረው የመንፈስ ግብር ነው ! [8]

መልካም አጋጣሚ ሆኖ **ፍቅር እስከ መቃብር** "ክብር ነክ" በሚል ክስ ተወንጅሎ ከበካዩ የተጠቀሰውን ዓይነት ሐሳብ ያሠፈሩ ገጾች በሳንሡር ጉጠት ያከመመዘዛቸው ነው ።

ባጠቃካዩ ሳንሡር ብቻውን መሠረታዊ የሀገር ችግር አይደለም። ቀጡን ያጣ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ሥርዓት ውካጅ ነው። የፖለቲካ ስልጣን በሕዝብ እጅ ሲደካደል ዴሞክራሲ ያብባልና አደንቋሪ የሆነው ሳንሡር ግባተ መሬት ያኒ ይፈጸማል።

በመጨረሻም ገሞራው (ኃይሉ ገብረ፡ዮሐንስ) "ነጸዱም ጠካቾች" በሚል ርዕስ ከጻፋት ግጥሚቸው፡-

"በሚደ እኖራለሁ የማርፍበት ባጣ፣
አልያም ከዱሬ እሆናለሁ ጦጣ፣
ካገር ግን አልወጣም የመጣ ቢመጣ፣
አልያም እካከሁ፤ካፈርሽ እያብቃኝ በጣም መሮኝ
ከሔጽኩ፤ጻግመኛ ካልመጣ።" [9] እንጸሎት በየጊዜው በተፈጠሩት ሰንካካ ስርዓቶች ምሬት ሰበብ ስንቱ ኢትዮጵያዊ ይሁን እስከመቸም ወደ ሀገሩ ካከመመከስ የወሰነው? እቶ ኃይሉ ከቻይና ከፍተኛ ትምህርት በኋላ ወደ ሰሚን አሚሪካ መምጣቱ ይነገራልና **በሰምና ወርቅ** መጽረክ ብቀታዎን እነጠብቃ!

## የግርጌ ማስታዎሻዎች፤

1. **ሰምና ወርቅ** ርዕሰ አንቀጽ፤ ቅጽ ፩ ቁጥር ፪፤ ሰኔ ፲፱፻፸፱ ዓም ገጽ ፬
2. ገሞራው ፤ **አዲስ ዘመን ጋዜጣ** ግንቦት ፳፪ ፲፱፻፺፪ ዓም ገጽ ፪
3. ጸጋዬ ገብረ፡መድህን፤ በስድስት ኪሎው ቀ.ኃ.ሥ ዩኒቨርስቲ ጸራሲው ሲያነብ የሰማሁት ጊዜውን፣(ዓመቱን ወራቱን) በትክክል አላስታውስም።

4. **ሰምና ወርቅ** ቅጽ ፮ ቁጥር ፪፤ ሰኔ ፲፱፻፸፱ ዓ.ም ገጽ ፬

5. ገምራው፤ **በረከት፡መርገም**፤ ነሐሴ ፲፱፻፲፯ ዓ.ም ገጽ ፲፯

6. እንደካይደኛው፤ ገጽ ፶፯

7. በዓሉ ግርማ፤ **ኦሮማይ**፤ አዲስ አበባ ፲፱፻፸፫ ገጽ ፲

8. ሐዲስ ዓለማየሁ፤ **ፍቅር እስከ መቃብር**፤ አዲስ አበባ ፲፱፻፶፲ ገጽ ፬፻፶፬።

9. ገምራው፤ ፍንዳታ፤ አዲስ አበባ ፲፱፻፲፯፤ ገጽ ፶፯

መስከረም ታደሰ (አልበርታ፤ካናዳ)

ለሰምና ወርቅ አዘጋጆች፡

፳፱ ዓመት የስደት ሕይወቴ ውስጥ እንደተመለከትኩት ስለኢትዮጵያ ባሕል፣ታሪክና ሥነ ጽሑፍ የዛሬው ትውልድ ቸልተኛነት ስካሳየ አዝን ነበር። ግን ያሁኑ እቅዳችሁ ይህን አቅጣጫ እንደሚለውጠው ተስፋ አለኝ። አጀማመራችሁ የሚያነቃቃ ነው ማለት ይቻላል።

መጽሐፍቶቼን ለኢትዮጵያ አንባቢዎች ጋር ለማስተዋወቅ ያላችሁን መልካም ፈቃድ ስለገለጣችሁልኝ ከልብ አመሰግናለሁ። እስካሁን ድረስ ብቻዬ ከመታገል በቀር ጥረቴን በመካፈል የሞራልም ሆነ የቁሳቁስ ድጋፍ ያበረከተኝ ሰው በጣም ዕፁብ ነው። እንደጠየቃችሁኝ ከመጽሐፍቶቼ አንዳንድ ቅጂ በተለየ ፖስታ ልኬያለሁ።

በቅንነት፡

ብርሃኑ፡ደንቄ።

ይድረስ ለሰምና ወርቅ አዘጋጅ፡-

እኔ ካሣሁን ነጋሽ የምባል ኢትዮጵያዊ ሰምና ወርቅን የመጀመሪያ እትም እንደ ጓደኛዬ በሆነ ኢትዮጵያዊ አማካኝነት አገኘሁ በታላቅ

ደስታና አክብሮት አንበቤዋለሁ።

ከሥራ አስኪያጅ ኮሚቴውና እንዲሁም ከአቶሙ መጸሬጃት እርዳታ ካደረጉት ኢትዮጵያውያን በሙሉ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። የጉዳዩ አስፈላጊነትና አሳሳቢነት በሁላችንም ውስጥ ያለ ነው። እናንተ ይህንን በማሰብ በጥሩ ሁኔታ የጀመራችሁት ስለሆነ ከመጽሔቱ ብቻ ሳይሆን ካሳቡ በወረቀት ላይ ከመስፈሩ መረዳት ይቻላል። ስለሆነም ጉስ በርቱ፣ አጀማመራችሁ የሚያስመሰግን ነው፣ ወደፊት እንዲቀጥል አደራ እላለሁ።

በየጊዜው የሚወጣውን እትም በማሕበርተኛነት እንዲደርሰኝ ስጠይቅ ከዚህ በፊት ከእትም አንድ (1) ጀምሮ የወጣውንም ከታች ባለው አድራሻዬ እንድትልኩልኝ እየጠየቅሁ አስፈላጊውን ወጪ ከእናንተ እንደወቀሁ በአስቸኳይ የምልክ መሆኔን በአክብሮት አስታውቃለሁ።

ከአክብሮት ጋር
ካሣሁን ነጋሽ (ኒው ዮርክ)

ነሐሴ ፯ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም

ከአዘጋጆች፡

"እንዴት እንገናኝ" እና "ምን እንወያይ" የሚሉ ባልጠፋበት ወቅት **የሰምና ወርቅ** በቀታ የውይይት መድረክን ሳያሰፋው አይቀርም። ስለሆነም አከም አቀፍተኛ የሆነው ኢትዮጵያዊ ስደተኛ የሚኪበት አካባቢ የሚያገናጠው ብቸኛነት እያዘገነነው በመጣበት በአሁኑ ሰዓት መጽሔቱ የሩቅ ከቅርብ መጣቀሚ፣ መገናኛ መወያያ ምዕራፍ መክፈቱ ዓቢይ አስተዋጽኦ አለው። በተከያሚ ባለፉት ፲ ዓመታት ውስጥ የፖለቲካ ማዕበል ያናጋው ዘሬ ፖለቲካ ሲነሳ የዘመዋል። ስለዚህ የሀገራችንን ሥነ-ፅሑፍ፣ ሥነ-ጥበብና ዕደ-ጥበብ ብቻ ሳይሆን ምጣኔ ሐብታዊ፣ ማህበራዊ ፣ባሕላዊ፣ ፖለቲካዊና ርዕዮት ዓለማዊ ሁኔታቸውንም በማንጸባረቁ "ትናንትናም እንደዚሁ" "ዛሬም ያው እንደነበር" በሚሉ ሆደ ባሻዎች ሰፈር ራሱን እንዴት እንደምትከሥት ማየቱ ያጓጓል። የሰው ልጅ

እንደ፡ኢውሮፓ፡አቈጣጠር፡በ1923፡ዓ.ም፡አሳተሟት፡ነበረ። (3) እኛም፡የእንደ፡ዐቢይ፡እውደ፡ቀመር፡ዘመን(እንደ፡ዓቢይ፡እውደ፡ቀመር፡532፡ዓመት፡ነው) የመጣውንና፡የከመጣውን፡ልዩነት፡ከሚያት፡እንደገቹከ፡ከሰምና፡ወርቅ፡አገባቦች፡እናቀርባለን። በተከየ፡አገባበውን፡የሚያውቁት፡አገባቦች፡በበከጠ፡እንዲሚያጠኑት፡እንገምታለን።

## የግዕዝ፡ሰነድ፡

በአኰቴት፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡

ዘንተ፡ሥርዓተ፡ዘሠርዓ፡ንጉሥነ፡ዘርአ፡ያዕቆብ፡ዘተሰምየ፡ቈስጠንጢኖስ፡ስምአመ፡ነገሠ፡በ፳ወ፪፡ዓመት፡ወዓመተ፡ምሕረቱኒ፡ስምአጸም፡እስከ፡አመ፡ተጽሕፈ፡ዝንቱ፡ነገር፡፲፻ወ፬፻፶ወ፯፡እንዘ፡ሀሎ፡ምድረ፡ክልአት፡አመ፳ወ፫፡ለወርኃ፡የካቲት፡ዘወሀቦሙ፡ምድረ፡ከመ፡ይስብኩ፡ወያስተራትዑ፡ካህ(ሚ) ናት፡ደቂቀ፡ከሚዐቀበ፡እግዚእ።

ወከፍሎሙ፡ከደብረ፡ማርያም፡ሰራዌ፡ወበጽርዋጌት፡ወባሕረ፡ማርያም፡ወዱርቢታ፡አኅያ፡በጊዳ፡ገምቢዳ፡ኀዘ፡ደሰዋ፡ተርዓ፡አሰውርታ፡ወምድረ ባርያ፡ዘዱበኔ፡ወክልኤ፡ማርያ፡

ወከፍሎሙኒ፡ከደብረ፡ቢዘን፡ሐማሴን፡ሐምብርት፡አስመራ፡ሰሐርት ወቀርት፡ባሕር፡አማባ፡ወዱርቢታ፡አብርሃም፡ወዋኪቶ፡

ወበከመ፡አስተካፈለ፡ዘንተ፡አኅጉረ፡ከሰቢስ፡ሃይማኖት፡
ይክፍሎ፡እግዚአብሔር፡ሐዩወ፡ከብዙኅ፡ዓመታት።
ወመንበረ፡ንግሥ፡ይረሲ፡ቀዋሚ። እስከ፡ይመጽእ፡በስብሐት፡
ወያጥፍእ፡ፀር፡ወጸካእቶ፡ዘበቀድቦት፡
በዝ፡ዓለም፡ወበዘ፡ይመጽእ፡ዓለም፡ይረስዮ፡ርእሰ፡ነገሥታት፡
ወየአጽዋ፡ከምኅሐ፡ደብረ፡ጽዮን፡ዘ፲፻፡ዓመት።
ወያግርክ፡እሞ፡ብእሲቶ፡ወውሉዶ፡በዘመንፈስ፡ቅዱስ። በረከት፡
ወለደ፡ትምህርቶሙ፡ውእቱ፡ከነቢያት፡ወሐዋርያት፡

ዘጸወን፡በአክናፈ፡ክልኤ ጽንገልናሃ፡ለእግዝእትነ፡(ማርያም)

እምአርዌ፡ምስሌት፡

ወዖኅብኦ፡ኵቱ፡እምገጸ፡ሞት፡

ከዓከሙ፡ዓከም፡ስሚን። ። ። ።

ዷቤ፡ንጉሥነ፡ዘርእ፡ያዕቆብ፡ኦስብእ፡ጸብረ፡ማርያም፡ወስብእ(ጸብረ) ቢዘን፡በእንተ፡ዘንቤክሙ፡ስብኩ፡ወመሀሩ፡እወረጽነ፡እምርእስነ፡ወኅበ፡ርእስክሙ፡እገባዕነ።

## ወደ፡አማርኛ፡ሲተረጎም፡

በአብ፡በወልድ፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡ምስጋና፡

ቈስጠንጢኖስ፡የተባለው፡ንጉሣችን፡በነገሠ፡በ22ኛው፡ዓመት ፤ ዓመተ፡ምሕረቱ፡ከዓለም፡ከአዳም፡ጀምሮ፡ይህ፡ጉዳይ፡እስከተፈጸመበት፡ድረስ፡6947፡ሲሆን፤ በምድረ፡ክልአት፡በነበረበት፡ጊዜ ፤ በየካቲት፡ወር፡በ27፡(ቀን) ይኸንን፡ሥራት፡ሠርቷል። የማዕቀበ፡እግዚአ፡ልጆች፡እንዲሰብኩና፡ሃይማኖትን፡እንዲያቀኑ፡የሰጣቸው፡መሬት(ከዚህ፡ቀጥሎ፡ያለው፡ነው)።

የደብረ፡ማርያሞች፡ድርሻ፡-ሰራዊ÷በጽርዋጊት፡-ባሕረ፡ማርያም÷ዱርቤታ፡አሳያ÷በጊዷ÷ገምዒዳ÷ኅዘ÷ደሰዋ÷ተርዳ÷አሰውርታ÷የዱብኔው፡ምድረ፡ባርያ÷ሁከቴ፡ማርያሞች(ነው)።

የደብረ፡ቢዘኖች፡ድርሻ፡ደገዋ፡ሐማሴን÷ሐምብርት÷አስመራ÷ስሐርት÷ወቀርት÷ባሕር፡አምባ÷ዱርቤታ፡አብርሃም÷ዋኪቶ፡(ነው)።

ሃይማኖት፡ከመስበክ፡እነዚህን፡አገሮች፡እንደካፈለ፡ .

እግዚአብሔር፡ከብዙ፡አመታት፡መኖርን፡ይክፈለው።

የንግሡን፡ዞፋንም፡በክብር፡እስኪመጣ፡ድረስ፡ቀዋሚ፡ያድርገው፡

ተቃዋሚውንና፡ጠላቶቹን፡በአንድ፡አፍታ፡ማጥፋት፡ያጥፋ(ለት)፡

በዚህ፡ዓለምና፡በወዲያኛውም፡ዓለም፡የንጉሦች፡አለቃ፡ያድርገው፡

ከአንድ፡ሺ፡ዓመቱ፡የደብረ፡ጽዮን፡የምሳ፡ገበታ፡ያብቃው።

እናቶን÷ሚስቱ÷ልጆቹን፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡በረከት፡ይባርክ(ከት)፡
እሱ፡የነቢያትና፡የሐዋርያት፡የትምህርት፡ልጃቸው፡ነው፡
በመቢታችን፡(በማርያም) በሁለት፡ጽንገልናዋ፡ክንፎች፡
ከአሳች፡ሰይጣን፡የተጋረደ፡ነው፡
እንዲሁም፡ከሞት፡ፊት፡ይሰውረው።
ከዓለመ፡ዓለም፡አሜን ። ። ። ።

ንጉሣችን፡ዘርአ፡ያዕቆብ፡"የጸብረ፡ማርያምና፡የ(ጸብረ) ቢዘን፡ሰዎች፡ሆይ÷ ስበኩ፡አስተምሩ፡በማለታችን(ኀላፊነቱን) ከራሳችን፡አውርደን፡ወደናንተ፡ራስ፡አስተላልፈናል፡" ብሏል ።፡

## ማብራሪያ፡

1·ሰነዱ፡የተገኘው፡አንድ፡ገጽ፡ላይ፡መደዳውን፡ተጽፎ፡ነው። "ደቢ፡ንጉሥን፡" ብሎ፡የሚጀምረው፡የመጨረሻው፡ዐረፍተ፡ነገር፡ብቻ፡ከቀረው፡ክፍል፡በአንድ፡መሥመር፡ፈንጠር፡ብሎ፡ተጽፏል። ለማንበብ፡እንዲመች፡በመሰለኝ፡በአጫጥር፡አንቀጾች፡ከፋፍየዋለሁ ንጉሡ፡የተመረቀበት፡ክፍል፡ቢት፡ሲመታ፡ስላየሁት፡እንደገጥም፡አጸጻፍ፡ቢጻፍ፡የተሻለ መሰለኝ።

2·በግዕዝ፡ውስጥ፡በማአዘናዊ፡ቅንፎች፡ያሉት፤ ለምሳሌ(ማርያም) (ማ) እና(ጸብረ) አሰነዱ፡ውስጥ፡የሉም። የሰነዱ፡ጸሐፊ፡የረሳቸው፡ናቸው፡በማለት፡እኔው፡በገዛ፡ፈቃዴ አክያቸዋለሁ። የማርያምን፡ስም፡እንኳ፡በኋላ፡በቀይ፡ቀለም፡ሊሞላው፡አስቦ፡ባዶ፡ቦታ፡ትቶለት፡ነበር፡እስቲያገኝ፡ድረስ፡ሲጠብቅ፡በዚያው፡ተረስቶ፡ቀርቷል። በብራና፡መጻሕፍት፡ውስጥ፡የአምላክና፡የጻድቃን፡ስሞች፡እንዳንዴም፡ቁጥሮች(አኀዞች) አብዛኛውን ጊዜ፡የሚጻፉት፡በቀይ፡ቀለም፡ነው። ታዲያ፡አንዳንድ፡ጊዜ፡እንደዚህ፡እየተረሱ፡ይቀራሉ። ስሞቹን፡እንኳን፡በግምት፡ለማወቅ፡ይቻላል። ቁጥሮች፡ሲረሱ፡ግን፡ነገር፡ይበላሻል። ለምሳሌ፡ቁጥሩ፡አንድ፡ታሪክ፡የተፈጸመበት፡ሊሆን፡ይችላል።

3·አማርኛው፡ውስጥ፡በቅንፍ፡የተጻፉት፡አማርኛው፡እንዲስተካከል፡ብየ፡እኔ፡የጨመርኋቸው፡ናቸው፡እንጂ፡አግዕዙ፡ሰነድ፡ውስጥ፡ተወዳዳሪ፡የላቸውም። ያልፈለገ፡ሊሰርዛቸው፡ይችላል።

አፄ፡ዘርአ፡ያዕቆብ፡ከጻበረ፡ጽዮን፡የምሳ፡ገበታ፡የማያምነውን፡ሁሉ፡ከሚገባው፡በካ ደ፡ይቀጡት፡ነበር። ጊዜውንም፡መጻሕፍቱን፡መርምረው፡ዘመኑን፡ሰፍረው፡ቈጥረው፡በ 7000፡ዓመተ፡ዓለም(ማለት፡ሰባተኛው፡ሺ፡አልቆ፡ስምንተኛው፡ሺ፡ሲገባ) ገደማ፡ነው ይሉ፡ነበረ። (16) በዚያን፡ጊዜ፡ሰው፡ሁሉ፡ከፍርሃት፡የተነሣ፡ንስሐ፡ገብቶ፡ስለሚጠ ባበቅ፡ኢትዮጵያ፡የሰላምና፡የፍቅር፡አገር፡ነበረች፡ብሎ፡መገመት፡ይቻላል። በዚያን፡ ጊዜ፡ይገዛ፡የነበሩት፡አፄ፡ናኦድ(1487-1500፡ዓ.ም፡=1494-1508A.D.) አንኮበር፡ አጠገብ፡በሐምሌ፡ወር፡የአይራራን፡ወንዝ፡አሻገራለሁ፡ሲሉ፡ውሀ፡ሙላት፡አጉሳቍሏ ቸው፡የነሐሴ፡ሥላሴ፡ዕለት፡መሞታቸው፡ይታወሳል። (17) በዚህ፡ምክንያት፡መስከረም ጠብቆኪካውን፡ዘመን፡ሳያዩ፡ስለቀሩ፡አግዚር፡አንደማራቸው፡ተቈጥሮላቸዋል።

11. ምርቃቱና፡ጸሎቱ፡ከዘርአ፡ያዕቆብ፣ ከእናታቸው፣ ከሚስታቸው፣ ከልጆቻቸው፡መሆኑ፡ ንጉሡ፡ከአንድ፡ሚስት፡የበለጠ፡እንደነበራቸው፡የሳይ፡ይሆን፡? ይኸን፡ያነሣሁበት፡ም ክንያት፡የዚያን፡ጊዜ፡ነገሥታት፡ብዙ፡ሚስቶች፡ነበራቸው፡የሚል፡ጽሑፍ፡ስላየሁ፡ነው።

ጌታቸው፡ኃይሌ፡
ሚኒሶታ፤ሰሜን፡አሜሪካ።
(ነሐሴ፡፫ ቀን፡፲፱፻፸፱ ዓ.ም)

## የግርጌ፡ማስታወሻዎች፤


1. A. Caquot, "Aperçu prèliminaire sur le Mashafa Tefut de Gechen Amba", Annales d'Ethiopie, vol. 1 (1955), ድጋሚ፡እትም፡Nendeln/Liechtenstein 1975, ገጽ 89-108.

10· Ignatius Guidi, Annales Regum Iyâsu II et Iyo'âs (Corpus Scriptorum Christianorum Orientalium, text.ser.alt., t.6) Lipsiae 1910, ገጽ፡218-219።

11·Perruchon, Les Chroniques, ገጽ፡47 = F.M.E. Pereira, Chronica de Susenyos,Rei de Ethiopia, vol. 2, Lisbon 1900, ገጽ፡626።

12· Merid Wolde Aregay, "Political Geography of Ethiopia at the Beginning of the Sixteenth Century", IV Congresso Internazionale di Studi Etiopici, Rome 1974, ገጽ፡616።

13· Taddesse Tamrat, Church and State, ገጽ፡275; Beckingham and Huntingford, Some Records, ገጽ፡97-102።

14· "ወገዩአት፡ወርኃ፡የካቲት፡አመ፳፡(=በዚያው፡የካቲት፡ወር፡3ቀን) ተሥዕረ፡(=ተጸፈረ፡) ወተበርበረ፡ግሼ(ን) ፡አምባ፡ነገሥት፡ወተረክበ፡በህየ፡(=እዚያም፡ተገኘ) ብዙኅ፡ከበሰ፡ሐሪር፡መዛግብተ፡ነገሥት፡ዘቀደምት፡ዘተዘገበ፡እሞዩኩና፡እምካስ፡እስከ፡መንግሥቱ፡ክክብነ፡ጸንገክ" M. Renè Basset, "Études sur l'histoire d'Éthiopie", Journal asiatique, 7/13(1881), ገጽ፡331።

15· Hillel Schwartz, "Millenarianism" (Mircea Eliade, ed.), The Encyclopedia of Religion, vol. 9 (1987), ገጽ፡521-532።

16. Getachew Haile, "The Cause of the Estifanosites: A Fundamentalist sect in the Church of Ethiopia", Paideuma, vol. 29 (1983), ገጽ፡ 108-109.

17. Sergew Hable-Selassie, "The Ge'ez Letters of Queen Eleni and Lebna Dingel to John, King of Portugal", IV Congresso Internazionale di Studi Etiopici, ገጽ፡ 551.

# ከመካው ዓለም የቀረበ የፊደል ገፀበረከት

ከተክከማርያም ኃይሌ

(ዋሺንግተን ዲሲ)

## 1· የፊደሎች አፈጣጠር እና የቅርፃቸው አመጣጥ። (አጭር መንደርደሪያ)

የሰው ልጅ አፉን ፈቶ እና አንደበቱን አቃንቶ የአስተሳሰብ ግንፋሎቱን ከመግለፅ የቃጣው ስእለፀሐፈት (pictograph) በሚባል ቅርፀነገር (ለምሳሌ በሬን በበሬ ስእል አስመስሎ በመንደፍ) ነበር። በስእለአሳብ (ideography) አማካይነትም (ለምሳሌ ሙቀትን በፀሀይ ንድፍ ስልጣንን በዘውድ ስእል በመጠቆም) አንዳንድ ሁኔታዎችን ያንጸረጸር ነበር።

ውሎ አድሮ ግን የስልጣን ጦራ ፍንጣቂ አያየ እና የኑሮውንም ጣእም እየቀመሰ ሲሄድ አመጀመሪያው የንቃተ-ህሊና እርከን ካይ ከመቆም በቃ። ከትውስታና ከመደጋገም ከሚያስቸግር ስድ አነጋገርም ተላቆ የተሰበጣጠሩ ፊደሎችን አጣል አየፈጠረና ቅርፃቸውንም በየዘመናቱ አያሻሻለ ተጨግጭ ፍሬአሳቡን በፅሁፈት በመመዝገብ ከትውልድ ወደ ትውልድ ማሸጋገር ጀመረ። ለምሳሌ የኛው ፊደል ከየት ተነስቶ የት እንደደረሰ ታሪክ ፀሀፊው አቶ ተከለፃድቅ መኩሪያ "የግብፅ-የሳባና የኢትዮጵያ ፊደሎች ማስታወሻ" በሚለው የ1950 (እ.አ.) ድርሰታቸው ገምግመውታል። እንደታዩአቸው ያህልም የፊደሎቹን ክፍል ብቻ በአንደኛው ንድፈቀጽ-ሰንጠረዥ አቅርቤላችሁአለሁ።

ሶስተኛ ሰያፍና (ግማሽ) ንኡስ ጭረት (\/)

አራተኛ ሰያፍ አቢያ ጭረት (\/)

ከምሳሌ የመጀመሪያው (ሀ) ሲፃፍ ከሁለት ቀዋሚ አቢያ ጭረቶችና

ከአንድ አግዳሚ ግማሽ ንኡስ ሰረዝ (ጭረት) (-) ጋር ተያይዞ ነው። ሁለተኛው (ካእብ) ድምፅም (ሁ) በግማሽ ቀኝ ጎኑ ላይ አግዳሚ ግማሽ ንኡስ ጭረት ተቀጥሎበት ራሱን ነፃ አውጥቶአል። ሶስተኛው (ሳልስ) ድምፅ (ሂ) በመጨረሻ ቀኝ ጎኑ ላይ ግማሽ ሰረዝ (‿) ተጥሎበታል። አራተኛው (ራብእ) ድምፅ (ሃ) በመጨረሻ ግራ ጎኑ ላይ ግማሽ ንኡስ ጭረት (-) ተቀጥሎበታል። አምስተኛው (ሀምስ) ድምፅ (ሄ) ደግሞ በመጨረሻው ቀኝ ጎኑ ላይ አግዳሚ ንኡስ ጭረትና (-) ቀዋሚ ንኡስ ጭረት (ı) ተጋጥመው (‿) ቀጥሎ ወደያው ያልቀለታል። ስድስተኛው ድምፅ (ህ) የካእቡን (የሁለተኛውን) ድምፅ ምልክት ይቀለብሰዋል። ከሰባተኛው (ሳብእ) ድምፅ (ሆ) የወጣለት ዘዴ የቀኙን ንኡስ ጭረት በግማሹ ከፍ መተው ነው።

አንድ ምሳሌ ልጨምር፡- አዲሱ (A) የተነደፈው ከሁለት ሰያፍ ሰረዞች ተገጣጥሞና ልክ በግማሽ ወገቡ ላይ አግዳሚ ንኡስ ጭረት ተሰምሮበት ነው።

እንግዲህ ይህ ከወደፊት የታጠው አዲስ ፊደል በአራት የሰረዞች (ጭረቶች) ደንብ ብቻ ስለተደነገገ ምቾቱን (ቀላልነቱን) እና ጠቀሜታውን ከማጤን ምንም ያህል ግንዛቤን አይጠይቅም። አሁን የምንገለገልበት ፊደላትንም ከብዥርዥርነትና ከስርአተ አልባነት ያገላግላል። ስለዚህም አባባልና ሁኔታ የመፅሄቱ አንባቢዎችና ሌሎችም አጥባቂ ተከራካሪዎች ግምገማቸውን አበርክቱበት።

የፊደሎቹ አጣጣል ግልፅም ቢመስል አንዳንድ ማብራሪያዎችን መስጠት ያገባኛል። የላቲኑ (A) እና የኛው (A አ) በመልክና ታሪክ አምብዛም አይራራቁም። የኛው (ሀ) እና የላቲኑ (H=ኤች) ሊመሳሰሉ ይፈልጉና አታችና

አወገብ ላይ በዋሉ ሰረዞች አሉያ ባለመሆን ብቻ ይለያያሉ። በተለዋዋጭም የላቲን (H=ኤች) የኛን (H=Z) ይመስላል። የኛው (በ) እና የላቲን (B) በትንሽ ርክርክነት ሊነጣጠሉ አይፈልጉም። የኛው አዲሱ (ከ) ወይም ነባሩ (ከ) ከላቲን (K) አምብዛም አይቀቀሩም። የኛው (ፀ) እና የግሪኩ (θ) ነፍስና ስጋ ናቸው። የኛው አዲሱ (ሠ) እና ነባሩ (ወ) ከላቲን (W) ጋር ፍቅረኞች ናቸው። ገፅታቸውም ይመሳሰላል። አዲሱ (ጠ) እና ነባሩም (መ) ከላቲን (m) ጋር ተጠጋግተዋል። የኛው (Λ) እና የግሪኩ (Λ) መንትያ ናቸው። የኛው አዲሱ (∇) እና የግሪኩ (Δ) ግልብጦሽ የሚጣጠቁ ይመስላሉ። የኛው (ተ) እና የላቲን (t T ) ዝምድናቸውን አበክረው ይዘውታል። የኛው (ገ) እና የግሪኩ (Γ) በሁዋላየሽ ጥሪ ጀርባ ከጀርባ ተሰጣጥተዋል። አዲሱ (I) ሁለቱን የላቲን (N) ሰረዞች ተቶ በሶስተኛ ቢተዘመድነት ገብቶአል። የኛን (L) ገልብጦ የላቲኑን ትንሽ (r) መስሎ ከቀጥያ አንዲያመች ተጀርጎአል። አዲሱ (Y) ነባሩ (የ) ከላቲን (Y) ጋር ተጣፍተዋል። ነባሩ (ፊ) በምንም ፈሊጥ ከቀጥያ የማያያመች በመሆኑ በቀርብ ዘመዱ በግሪኩ (ф) ተመስሎ ነባሩን የኛን (ቀ) አጣፍቶ ተከውሶአል። የኛው (ፕ) እና የላቲን (P) ግቁዋቁዋም ይመሳሰላሉ።

የአረቢ ፊደል በመገል የታወቀት እነ ሸ-ዠ-ጨ-ጀ-ቸ በቀላል ምልክት ሽ-ዥ-ጭ-ጅ-ች- ተገላግለዋል። ፐ እና ቸ የኛው ቀዋንቁዋ መገልገያ ህርመቶች ይመስላሉ።

## 5· ከህልውና የተሻሩ ፊደሎች

ሐ ኀ ኸ የ (ሀ) ሞክሼ በመሆናቸው
ሠ የ (ሰ) ሞክሼ በመሆኑ
ጸ የ (ፀ) " "
ዐ የ (አ) " "

በተጨማሪም እንደዚያው ሲባዝኑና ሲንዛዙ የኖሩት ዲቃላ ፊደሎች ምንም አገልግሎት ስለሌላቸው በፍፁም ከህልውና ተሰርዘዋል። ለምሳሌ "ቋንቋ" "ሟሟ" የመሳሰሉትን ፀያፍ አፃፃፎች "ቁዋንቁዋ" "ሙዋሙዋ" ብሎ በዝርዝራቸው ማስፈር ይቻላልና ከነዝርያቸው ከህልውና መውጣት ይኖርባቸዋል።

## 6· መደባቸውን ያንሸራሸሩ ፊደሎች

እመቺ ምቶች ቀርበውላቸው መደባቸውን ያንሸራሸሩ ፊደሎች የሚከተሉት ናቸው፡-

| | |
|---|---|
| ሽ በ (ሰ) ተተክቶአል | ቸ በ (ተ̄) ተተክቶአል |
| ከ " (h) " | ጰ " (T̄) " |
| ኸ " (H̄) " | ነ " (l) " |
| ጠ " (m̄) " | ኘ " (Ť) " |
| ጸ " (▼) " | ረ " (r) " |
| ፀ " (▼̄) " | የ " (Y) " |
| አ " (A) " | ፈ " (ф) " |
| | ቨ " የካቲትን V ድምፅ ይወክላል። |

## 7· መደምደሚያ፡-

ይህ ከወደፊት የታጠው አዲስ ፊደል እንኳዋን ከኛ ቀርቶ ከአፍሪካና ከመላው አለምም ጠቀሜታው በጉልህ የሚታይ ነውና መቀደትና መራባት አለበት ብዬ አምኔን ጥዬበታለሁ። ምክንያቱም በሁዩክድምፅ (vowel) በድምፅ ፍካ (pronunciation) አዋጅ የሚነገር ቀዋንቀዋ ሁሉ እንደቀበቶ እድሚን ሙሉ ስለሚያከፋ ነው።

ይህ አዲሱ ፊደል ታፍሶ የማያልቅ የወርቅ ማእድን ነው። ያገሩን ሰርደ ባገሩ በሬ የሚለው ምሳሌ እዚህ ላይ በጣም ያዋጣል። እንግዲህ ገልመጥ



* ይህ ፡ ፊደል ፡ የተቀዳው ፡ [illegible] ፡ ከ[illegible] ፡ የታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ [illegible] ፡ በ[illegible] ፡ ከ[illegible] ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ ነው ፡፡

፲፰ ፡ ኀጽሬ-ቀጽ

# የወደፊቱ ፊደል

(አራተኛ ገፀገጸፍ)



1
2
3
4
5
6
7
8
9
10
11
12
13
14

# የሁኑ ፊደል

ሀ ሁ ሂ ሃ ሄ ህ ሆ (ሐ ኀ ኸ)

በ ቡ ቢ ባ ቤ ብ ቦ

ሰ ሱ ሲ ሳ ሴ ስ ሶ (ሠ ሡ)

ሸ ሹ ሺ ሻ ሼ ሽ ሾ

ከ ኩ ኪ ካ ኬ ክ ኮ

ቀ ቁ ቂ ቃ ቄ ቅ ቆ

ዘ ዙ ዚ ዛ ዜ ዝ ዞ

ዠ ዡ ዢ ዣ ዤ ዥ ዦ

ፀ ፁ ፂ ፃ ፄ ፅ ፆ

ጠ ጡ ጢ ጣ ጤ ጥ ጦ

ጨ ጩ ጪ ጫ ጬ ጭ ጮ

ወ ዉ ዊ ዋ ዌ ው ዎ

መ ሙ ሚ ማ ሜ ም ሞ



Boston, MA USA 1983

28 x 7 = 196